# ለወላጆችና ለተማሪዎፕች የወጣ ማስታወቂያ
# በአንቀጽ ቁጥር 504 የተሰጡ መብቶች
# (ፎርም 504-1)

The Rehabilitation Act of 1973, ውስጥ "Section 504," ተብሎ የሚጠራው ዓንቀጽ ማዳላትን ለመቃወም በአሜሪካ ኮንግረስ የወጣ ሕግ ነው።የህጉ ዋና ዓላማ ማዳላት እንዳይደረግ ለመከላከልና የአካል ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች ለሌሎች ማለት አካለ ስንኩል ላልሆኑ ተማሪዎች የሚሰጥ የትምህርት ዕድልና ሌሎች ጥቅሞች በእኩልነትና ያለማዳለት መሰጠቱን ለማረጋገጥ የወጣ ነው።

ስለዚህ ይህ ጽሑፍ በዓንቀጽ (Section) 504 መሰረት ያለዎትን መብት ለማስታወቅ የወጣ ነው። ጽሑፉ Individuals with Disabilities Education Act ("IDEA") ላይ የተጻፈው ልዩ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው (አካለ ስንኩላን) ለሆኑ ተማሪዎች የሚሰጠውን አገልግሎት የሚመለከት አይደለም። የአካል/የአእምሮ ስንክልና ያላቸው ተማሪዎችና ወላጆቻቸው ያላቸው መብት እንዲረጋገጥ የወጣው ህግ "Individuals with Disabilities Education Act (IDEA)" በስተይቱ ውስጥ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት ማለት "Office of the Superintendent of Public Instructions ("OSPI) ባለው "Notice of Special Education Safeguards for Students and Their Families" በሚል ስር ተጽፎ ይገኛል። የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ የተወሰነ የአካል ወይም የአእምሮ ስንክልና(ጉድለት) ስላላቸው ለህይወት አስፈላጊ ከሚባሉ ተግባሮችን ማከናውን የማይችሉ ነገር ግን በ "IDEA" ለአካለ ስንኩላን ተማሪዎች በተደነገገው ሕግ መሰረት ብቁ ላልሆኑ በዓንቀጽ (Section) 504 መሰረት ያላቸውን መብት ለማሳወቅ የወጣ ነው።

የፌደራል ሕጎችና ደንቦች ለተማሪዎችና ለወላጆቻቸው የሚከተሉት መብቶች ሰጥቷቸዋል፡

1. የሲያትል ትምህርት ቤቶች መምሪ (Seattle School District) በዓንቀጽ 504 መሰረት ያላችሁን መብት የማሳወቅ ግዴታ አለበት። የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ስለ እነዚህ መብቶች ለማሳወቅ ነው።
2. ልጅዎ ባለው/ባላት ስንክልና ምክንያት የትምህርት መምሪያው በሚሰጣቸው የትምህርት ፕሮግራሞች ያለ አድልዎ ለመሳተፍና ለመጠቀም መብቱ/ቷ ነው።
3. የትምህርት መምሪያው ስለ ልጅዎ ምደባ፣ ግምገማና(ምርመራ) ማንነትን የመለየት የሚመለከት እርምጃ ከመውሰዱ በፊት አስቀድመው ለማወቅና ማስታወቂያ ለምግኘት መብትዎ ነው።
4. ለልጅዎ በዓንቀጽ (Section) 504 መሰረት ምደባ ወይም ሌላ ለውጥ ከመደረጉ በፊት ምርመራ እንዲደረግለት መብቱ ነው። በልጅዎ ላይ በተደረገው የመጀመሪያው ግምገማ ወይም ምርመራና ምደባ ላለመቀበል መብትዎ ነው።
5. ልጅዎ ነጻና ተገቢ ("FAPE") የመንግስት(Public)ትምህርት እንዲሰጠው መብትዎ ነው። ይህምም ማለት ልጅዎ ዓቅሙ(ችሎታው) እስቀፈቀደ ድረስ የአካል ስንክልና ከሌላቸው ሌሎች ተማሪዎች ጋር መማርን ይጨምራል። በተጨማሪም የትምህርት መምሪያው በሚሰጣቸው የትምህርት ዕድሎችና ሌሎች አገልግሎቶች ለልጅዎም በእኩልነትና ያለ ማዳላት፣ በነጻና ማለት ያለ ክፍያ( አካለ ስንኩል ያልሆኑ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው የሚከፍሉት ክፍያ ከሌለ በስተቀር) አገልግሎት የማግኘት መብትዎ የተጠበቀ ነው።
6. ልጅዎ አካለ ስንኩላን ያልሆኑ ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው ቦታዎችና የሚሰጧቸው አገልግሎቶች የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው።
7. ከተለያዩ ምንጮችና ልጅዎን ከሚያውቁ ሰዎች በተገኘው ግምገማና ምርመራ መሰረት በልጅዎ ላይ የተደረጉትን ግምገማዎች፣ የተገኙት መረጃዎችና የምደባ ምርጫዎችን ለመመርመር፣ ግምገማ ለማካሄድና የተደረገው የትምህርት ምደባው እንዲታይ ለማድረግ መብትዎ የተጠበቀ ነው።
8. ልጅዎ በትምህርት መምሪያው የሚሰጡ አካዳሚያዊ ያልሆነና ሌሎች ፕሮግራሞች በእኩልነት የመሳተፍ ዕድል እንዲያገኝ መብትዎ የተጠበቀ ነው።

9. **የልጅዎን የትምህርት ውጤት የያዘ ሪከርድ የማግኘትና ሪከርዱን የመመርመር መብትዎ የተጠበቀ ነው። እንዲሁም ስለ ሪከርዱ የተሰጠውን መግለጫና ትርጉም ለትምህርት መምሪያው ለሚያቀርቡት ጥያቄ ተገቢ መልስ ለማግኘት ያለዎት መብት የተጠበቀ ነው።**

10. **የልጅዎ የትምህርት ሪከርድ የተሳሳተ፣ የሚያደናግርና እንዲሁም የልጅዎን ሪከርድ በሚስጥር እንዲታቀብ ያለውን መብት የሚጻረር ነው የሚል እምነት ካለዎት የትምህርት መምሪያውን እርማት እንዲያደርግና የተሳሳተውን እንዲያስተካክል የመጠየቅ መብትዎ የተጠበቀ ነው። የትምህርት መምሪያው ላቀረቡት ጥያቄ አልቀበልም ካለ በሕግ** "Family Educational Rights and Privacy Act ("FERPA")"**መሰረት መምሪያውን መክሰስ ይችላሉ።**

11. **የትምህርት መምሪያው ስለልጅዎ ያደረገው ምርመራ፣ ማንነት የመለየትና የትምህርት ምደባ ከመምሪያው ጋር የመደራደርና ጉዳዩን በአስታራቂ ወይ ዳኛ ወላጅና የሚወክላቸው ጠበቃ በሚገኙበት እንዲታይ የመጠየቅ መብትዎ የተጠበቀ ነው።**

12. **የትምህርት መምሪያው ስለልጅዎ ያደረገውን ግምገማ፣ ማንነት የመለየትና የትምህርት ምደባ ካልተስማሙበትና ተቃውሞ ለማቅረብ ከፈለጉ ኬሮል ሩሲሞቪች** (Carole Rusimovic) **ለምትባል ለዓንቀጽ** (Section) 504 **ፕሮግራም አስተባባሪ፣ ቀጥሎ በተጻፈው አድራሻ** ( MS 32-151, P.O. Box 34165, Seattle, Washington 98124-1165 **የአቤቱታ መጠየቂያ ቅጥ** 504-7 **(**Request for a Hearing Form 504-7) **በመተቀም በጽሑፍ ማመልከት አለብዎት። ጽሑፉ ከደረሰ በኋላ ጉዳዩ በአስታራቂ ዳኛ የሚታይበት ቀን፣ ሰዓትና ቦታ የሚነግር ጽሑፍ ይደርስዎታል።**

13. **አስታራቂ ሆኖ ጉዳዩን ያየ ዳኛ የሰጠውን ውሳኔ ካልተስማሙበት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ንደገና እንዲያየው የመጠየቅ መብት አለዎት። ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ የርስዎ ሐሳብ ተቀባይነት አግኝቶ ለእርስዎ ከተፈረደ በፍትሐ-ብሄር ሕግ መሰረት ለጠበቃ የከፈሉትን ወጪ የትምህርት መሪያው እንዲከፍል የመጠየቅ መብት አለዎት።**

14. **ያለዎትን ቅሬታ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ለሚመለከት ለፌደራል መንግስት በትምህርት መምሪያ ስር የሰዎች መብት ጥበቃ ጽ/ቤት(** U.S. Department of Education's Office for Civil Rights) **ወይም ለፌደራል ፍርድ ቤት የማቅረብ መብትዎ የተጠበቀ ነው። በስያትል የሚገኘው የፌደራል የትምህርት መምሪያ የሰው መብት ጥበቃ ጽ/ቤት አድራሻ** :

    U.S. Department of Education
    Office of Civil Rights
    915 Second Avenue, Room 3310
    Seattle, Washington 98174-1099
    Phone: (206) 607-1600
    Website: www.ed.gov/OCR
    Email Address: OCR.seattle@ed.gov